
# ጓድ ሙሉጌታ መንገሻ ዓለሙ



ጓድ ሙሉጌታ መንገሻ የተወለደው ሰኔ 6 ቀን 1946 ዓ.ም. (June 13, 1952) ከአቶ መንገሻ ዓለሙና ከወይዘሮ በዛብሽ ወርቅ ስዩም በጎጃም ክፍለሀገር በባህር ዳር አውራጃ ሜጫ ወረዳ ሲሆን የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በመራዊ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በ ጣና ሐይቅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠናቋል።

**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email ESPIC@aol.com**
**Website WWW.EPRP.com**

**EPRP**
**BP 30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**

ጓድ ሙሉጌታ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (በኢሕአፓ) አማካይነት እየተካሄደ የነበረውን ትግል የተቀላቀለው በ1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እድሜው ገና ወጣት በነበረበት ወቅት ነው።

በከተሞች አካባቢ መጀመሪያ በወጣት ክንፉ ከዚያም በፓርቲው መዋቅር በመታቀፍና በድርጅታዊና ቅስቀሳ ሥራዎች ላይ በመሳተፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። ለሕዝብ መብትና እኩልነት እንዲሁም አንድነት የጀመረውን ትግል ለመቀጠል የኢሕአፓ ሠራዊትን ኢሕአሠን ተቀላቅሎ ታግሏል። በኢሕአሠ ውስጥ በበርካታ የጦር ግምባሮች በጀግንነት የተሳተፈ ሲሆን በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎችም ተመድቦ ኃላፊነቱን በሚገባ ተወጥቷል።

ጓድ ሙሉጌታ በ1980ዎቹ እንደብዙዎቹ ወደ አሜሪካ የመጣ ቢሆንም ከድርጅቱ ጋር የነበረውን ትስስር ወዲያውኑ በመቀጠል ባለበት ሆኖ ትግሉን ለማፋፋምና ለማጠናከር ጥሯል። የዛሬ አምስት ዓመት በሞት ከተለየን ከጓድ አስማማው ጥሩነህና ከሌሎች የኢሕአፓ አባላት ጋር በመሆኑ በሚኖርበት በሲያትል አካባቢ ወገኖች ስለአገራቸው ጉዳይ እንዲሰባሰቡና ለትግሉ ተጨባጭ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል።

ጓድ ሙሉጌታ በሰሜን አሜሪካ የኢሕአፓ ቅርንጫፍ መዋቅር ውስጥ በተለያዩ ኃላፊነቶች ሠርቷል። በሰሜን አሜሪካ የኢሕአፓ ከፍተኛው የአመራር አካል የሆነው የኢሕአፓ አህጉራዊ ኮሚቴ አባል በመሆን ተመርጦ ለረጅም ዓመታት ያገለገለ ከመሆኑ በላይ የኮሚቴው ጸሐፊና አገናኝ በመሆንም ለተወሰኑ ዓመታት ሠርቷል።

በተጨባጭ ለትግሉ ካበረከታቸው አስተዋጽኦዎች ሌላ ጓድ ሙሉጌታ መንፈሰ ጠንካራ የነበረ ሲሆን ችግርና መከራ፤ ውጣ ውረድና ፈታና የማይበግረውና ተስፋ የማያስቆርጠው ብሩቱ ሰው ነበር። በተለያዩ ጊዜያት በትግሉና በድርጅቱ ላይ ደርሰው የነበሩ ፈተናዎችን ከሌሎች ጓዶች ጋር በመሆን ተቋቁሞ በጽናት ትግሉን በመቀጠል ማንነቱን ያስመሰከረ ጓድ ነው።

# *የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)*
*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

ጓድ ሙሉጌታ አምኖበት ሲታገልለት በነበረው ዓላማ እንዲሁም በመርህና በድርጅታዊ አሠራር ላይ የተስተካከለ አመለካከትና ግንዛቤ ነበረው። ዓላማውን የሚያፋልሱ መርህና አሠራርን የሚሸረሽሩ ባጠቃላይም ሕዝባዊ ትግሉን የሚያዳክሙ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት ያለማወላወል ታግሏቸዋል፤ ተጋፍጧቸዋል።

ጓድ ሙሉጌታ ደግና ሩህሩህ ነበር። ለተቸገሩና እርዳታ ለሚፈልጉ ወገኖች በቅድሚያ ደራሽ ነበር። ለሰው ችግር ዘወትር የሚጨነቅና የሚጠበብ ነበር፡፡ ከማንኛውም በላይ ግን ጓድ ሙሉጌታ አገሩን በጽኑ የሚወድ ዜጋ ነበር። የሕዝቡ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶቹ የተጠበቀባት፤ የሕግ የበላይነት የሰፈነባት፣ የሕዝብ የሥልጣን ምንጭነት የተረጋገጠባት፤  ሰላም አግኝታ በብልጽግና የዳበረች አገር ለማየት የዘወትር ምኞቱና ህልሙ ነበር። ህልሙና ምኞቱን እውን ለማድረገም የግል ጥቅሙንና ምቾቱን አሳልፎ በመስጠትም ሆነ ህይወት ሊያስከፍል በሚችል ትግል ውስጥ በመሳተፍ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። እስከ ህይወቱ ፍጻሜም ድረስ ሲታገል ቆይቷል።

ለአገርና ለወገን መታገል ክብርና ጸጋ ሲሆን በማናቸውም ጊዜ በመልካም ሊነሳ የሚችል የዘላለም ቅርስ ነው። ዛሬ ጓድ ሙሉጌታ ከእኛ በመለየቱ ብናዝንም በህይወቱ እያለ የሰራቸው ሥራዎችና ያበረከታቸው አስተዋጾዎች ህያው ሆነው ይኖራሉና ጓዶቹና ቤተሰቦቹ በዚህ ሊጽናኑ ይገባል።
ለውድ ባለቤቱ ለወ/ሮ ሀረግ ለልጆቹ ለስዩም ሙሉጌታ፤ ለቤዛዊት ሙሉጌታ፤ለቤተ ልሄም ሙሉጌታና ለልዑል ሙሉጌታ እንዲሁም ለቤተሰቦቹና ለቅርብ ጓዶቹ መጽናናትን እንዲሰጣቸው እንመኛለን።

ኢሕአፓ

**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email ESPIC@aol.com**
**Website WWW.EPRP.com**

**EPRP**
**BP 30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**